# መመሪያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY

---

**ተዛማጅ መመሪያዎች/ደንቦች፡-** ACA, JEA-RB, JEA-RC, JEA-RD, JED-RA, JEE, JEE-RA, KLA, KLA-RA
**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-** ዋና የአካደሚ ኃላፊ

## ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ

**ሀ. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ ውጤታማ/ገቢራዊ የሚሆን፣ በብቃትና ቅልጥፍና፣ እና ፍትኃዊ/ሚዛናዊ የመግቢያ ሂደት ብቃት ላላቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች በሙሉ እና በካውንቲው ነዋሪ ለሆኑ እና በካውንቲው ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች በፌደራል እና በስቴት ህግ መሠረት የመግቢያ መስፈርት ማዘጋጀት።

**ለ. ጉዳዩ**

ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ማለት የዩ.ኤስ. ዜጋ ቢሆንም/ባይሆንም፣ በወቅቱ የትምህርት ዓመት ሴፕቴምበር 1 ላይ ቢያንስ አምስት ዓመት የሞላው/ት፣ እና ከ20 ዓመት እድሜ በታች ማለት ነው።

ብቁ ተማሪማለት፣ የዩ.ኤስ ዜጋ ቢሆንም/ባይሆንም፣ በአብዛኞቹ የእድሜ ክልል ማለትም (18) የደረሰ/ች፣ ወይም 18 ዓመት እድሜ ሳይደርስ በፊት ራሱን እንዲችል የተደረገ (ራሷን እንድትችል ነፃ) ነገር ግን በትምህርት ዓመቱ የመጀመሪያው ቀን ከ20 ዓመት እድሜ በታች ማለት ነው።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች እዚህ ትምህርታቸውን ለመከታተል የሚፈልጉበት ሁኔታዎች ይኖራሉ፣ ስለሆነም የነዋሪነት እና የትምህርት አከፋፈል ጉዳዮች በግልጽ መነደፍ አለበት።

**ሐ. አቋም**

1. ቦርዱ የነዋሪዎቹን ነፃ የህዝባዊ ትምህርት መብት ይደግፋል።

   a) Bona fide residence ማለት ትክክለኛ መኖሪያ መሆኑ በተአማኒነት የሚጠበቅ ሲሆን፣ ለጊዜያዊ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ነፃ ትምህርት ለማግኘት ዓላማ የተመሠረተ ነዋሪነትን አይጨምርም። ይሁን እንጂ፣ አሁን ባለው የመኖሪያ ቦታ ላልተወሰነ ጊዜ ወይም በቋሚነት የመኖር ዓላማ የግድ አስፈላጊ አይደለም። የአንድ ግለሰብ እውነተኛ/ትክክለኛው የመኖሪያ ቦታ እውነታው በየግል ሁኔታ ላይ ይወሰናል።

      (1) በአንፃሩ ማስረጃ ለማቅረብ ካልተቻለ ግን፣ በትክክለኛው የመኖሪያ ቦታ ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ እንደ ... ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡-

         (a) የተማሪው(ዋ) ወላጆች/አሳዳጊዎች የታወቀ (ትክክለኛ) የመኖሪያ ቦታ።

(b) ወላጆቻቸው ተለያይተው የሚኖሩ ከሆነ፣ ትክክለኛ መኖሪያ ቦታ የሚወስነው ወላጅ በሚኖርበት መኖሪያ ብቻ፣ ወይም ተማሪው(ዋ) አብሮ የሚኖርበት ህጋዊ ጥገኝነት የተሰጠው ወላጅ ነው።

(2) ተማሪው(ዋ) ከወላጆቹ/ከአሳዳጊዎቹ ጋር ትክክለኛ የነዋሪነት ህጋዊ መብት ሊኖረው(ሊኖራት) የሚችለው በተናጠል ይሆናል።

b) ወላጆቻቸው ኑሮአቸውን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ መስርተው ነዋሪዎች የሆኑ፣ የዩ.ኤስ. ዜጎች ወይም ዜጋ ያልሆኑ ነዋሪ ተማሪ እንደሆኑ ይቆጠሩና በ MCPS በነፃ ትምህርት ያገኛሉ።

c) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ነዋሪነቱ(ቷ) ከተረጋገጠ ሞግዚት ጋር በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አብሮ የሚኖር/አብራ የምትኖር ተማሪ እንደ ነዋሪ ተማሪነት ይቆጠራል እና በ MCPS የትምህርት ክፍያ ሳይከፍል/ሳትከፍል ለመማር ይችላል/ትችላለች።

(1) ሞግዚትነት የተገኘበት ምክንያት ተማሪውን/ተማሪዋን በሚመለከቱ ምክንያቶች ከሆነ፣ እና፣

(2) ትምህርት ቤት እዚህ መከታተል ዋነኛው ምክንያት ሳይሆን ወይም ስለሚመለከታቸው ሰዎች አመቺነት ካልሆነ።

d) የዩ.ኤስ ዜግነት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፣ ነዋሪነታቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ የተመሠረተ ብቃት ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ፣ እንደ ነዋሪ ተቆጥረው ወደ MCPS በነፃ ይገባሉ።

e) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቤት አልባ የሆኑ ብቃት ያላቸው ተማሪዎች በስቴት እና በፌዴራል ሕግ መሰረት ይመዘገባሉ/ይገባሉ።

2. ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች ምዝገባ

በወላጆቻቸው/በሞግዚቶቻቸው አማካይነት ወይም ራሳቸውን ችለው በቋሚነት ነዋሪነታቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ያልሆነ ተማሪዎች፣ በካውንቲው ነዋሪዎች ባለመሆናቸው በዚህ የፖሊሲ ሠነድ ላይ ልዩ አስተያየት ካልተሰጠበት ወይም በሚተገበር ደንብ ላይ ካልተገለጸ በስተቀር የትምህርት ክፍያ መክፈል ይኖርባቸዋል።

a) ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች በ MCPS ገንዘብ ከፍለው ለመማር ፈቃደኛ ቢሆኑም እንኳ ት/ቤት የመግባት ጥያቄአቸው ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል።

b) ነዋሪ ያልሆነ(ች) ተማሪ በተለይ ወደ አንድ ት/ቤት ለመግባት ሊያመለክት/ልታመለክት ይ(ት)ችል ይሆናል፣ ነገር ግን ወደተጠየቀው ት/ቤት መግቢያ የመፍቀድ ውሳኔ የመስጠቱ ስልጣን የ MCPS ነው።

c) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ያልሆነ(ች) ነገር ግን በሜሪላንድ ስቴት ሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲዎች በቡድን ቤት በጥገኝነት ተዳብሎ የሚኖር፣ ወይም ህጋዊ የሆነ ዘመድ በመጠጋት የሚኖር/የምትኖር፣ ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ በ Section 4-122 or 4-122.1 of the ducation Article of the Annotated Code of Maryland ድንጋጌ መሠረት፣ በካውንቲው ነዋሪነት እንደሌለው/እንደሌላት ተደርጎ ስለሚገመት፣ MCPS ትክክለኛውን የትምህርት ወጪ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት ቤት ካስገባው ሌላ አካል፣ ከሜሪላንድ ስቴት፣ ወይም ከስቴት ውጪ ከሆነ ኤጀንሲ ማስከፈል ይችላል።

3. የትምህርት ክፍያ

a) የክፍያው መጠን የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ በሚያቀርበው አስተያየት መሠረት በየዓመቱ በትምህርት ቦርድ ይወሰናል።

b) ስለ ትምህርት ክፍያ ልዩ ሁኔታዎች/Exceptions

(1) የተማሪዎች ልውውጥ (J-1) በካውንስል የትብብር ተሳትፎ የፀደቁ በዓለም አቀፍ ትምህርታዊ ፕሮግራም የተሳትፎ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ጉዞዎችን ተግባራዊ የሚድረጉ።

(2) ከወላጅ/አሳዳጊ፣ ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ በትክክለኛ ማስረጃ የሚረጋገጥ የትምህርት ክፍያን ለመሠረዝ የሚያስችል ያልተለመደ እና በጣም ከባድ ክስተት።

(3) በካውንቲው ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ(ች) ተማሪ የይግባኝ ውሣኔ በመጠባበቅ ላይ መኖሩን የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ በታሳቢነት እንዲቆይ የፈቀዱ ከሆነ (አግባብነት ካለው)።

c) የትምህርት ቤት የበላይ ተቆጣጣሪ፣ ነዋሪ ያልሆነ(ች)ተማሪን ክፍያ በሚመለከት የወቅቱን ችግር ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት መሠረዝ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በመመርኮዝ ተገቢውን የመወሰን ሂደት መመሪያ ደንቦችን ያጸድቃል። እያንዳንዱ የነዋሪነት ወይም የትምህርት ክፍያ ስረዛ በየዓመቱ እንደገና ይገመገማል።

4. የነዋሪነት ማረጋገጫ ተግባራት

ትክክለኛ የመኖሪያ ሥፍራ የሚያመለክቱ ማስረጃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት በወላጅ/በአሳዳጊ ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ላይ ነው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ማስረጃዎች የነዋሪነት ቦታን ያመለክታሉ፣ ይሁን እንጂ፣ MCPS ተቃራኒ የሆኑ ማስረጃዎችን ካገኘ፣ ይህ ውሳኔ ሊነሳ (ሊቀለበስ) ይችላል። ከግለሰብ ማረጋገጫ በተጨማሪ፣ MCPS በክፍል-ደረጃ ወይም ትም/ቤት አቀፍ የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ የማጣራት መብት አለው።

5. ኃላፊነቶች

a) ወላጆች/ሞግዚቶች ወይም ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ቋሚ የመኖሪያ አድራሻቸውን ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ያለመሆናቸውን ማረጋገጫ በ MCPS ለመመዝገብ/ለመግባት እንደቅድመ ሁኔታ ቅጽ የመሙላት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በተጨማሪ፣ በዚህ መግለጫ ተማሪው(ዋ) በካውንቲው ያልኖረበት/ያልኖረችበት ጊዜ ምንም እንኳ የነዋሪነት ሁኔታ መጣራት ያለበት ከመጀመሪያ የምዝገባ/የመግቢያ ወቅት ቢሆንም የትምህርት ክፍያ እንደሚከፈል መረጋገጥ አለበት።

b) የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ በ MCPS ለመመዝገብ/ለመማር የሚፈልጉ ተማሪዎችን የመኖሪያ አድራሻ ሁኔታን የመወሰን ደንቦችን በማውጣት ይተገበራል። እነዚህ መመሪያዎች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወይም በአሜሪካ ትምህርት ቤት ውስጥ ያልተማሩ ተማሪዎችን፣ በአሜሪካ የመከላከያ ዲፓርትመንት ወይም በውጭ የሚገኙ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ ባለፉት ሁለት ዓመታት በማንኛውም ጊዜ ያልተማሩ ተማሪዎችን ያካትታል።

6. ይግባኞች

   በዚህ ፖሊሲ እና ማንኛውም የአፈጻጸም ደንቦች ላይ የተደረጉ ውሳኔዎችን በ MCPS Regulation KLA-RA መሠረት ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል፣ ለህዝብ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት። የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ/ተወካይ፣ ሱፐርኢንተንዳንቱን በመወከል ስለመኖሪያ አድራሻ እና የትምህርት ክፍያ ቅሬታዎችን እና አቤቱታ የሚሰማ እና የውሳኔ አስተያየቶችን ለሱፐርኢንተንደንቱ/ተወካይ የሚያቀርብ ኃላፊ/ተጠሪ ሊመደብ ይችላል።

D. **ተፈላጊ ውጤት**

ገቢራዊ የሆነ/የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ የሚችል፣ በብቃትና በቅልጥፍና ውጤታማነት ያለው፣ እና ፍትኃዊ የሆነ የመቀበያ/መመዝገቢያ ሂደት በነፃ ህዝባዊ ትምህርት ለማግኘት ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን ሙብት ያገናዘበ፣ አግባብነት ሲኖር ስለትምህርት ክፍያ፣ እና ለመማር የመመዝገብን መሰናክሎች መቀነስ።

E. **ግምገማና ዘገባ**

1. የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ በካውንቲው ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎችን የትምህርት ክፍያ መጠን በየዓመቱ ቦርዱ እንዲያፀድቅ ይጠይቃል እናም ስለክፍያ ዝርዝር መረጃ እና ክፍያ እንዲሠርዝላቸው የሚጠይቁ እና የተፈቀደላቸው ተማሪዎችን መረጃ ለቦርድ ያቀርባል።

2. ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ክለሳ ይደረጋል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** የሜሪላንድ ማብራሪያ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ § 4-122፣ 4-122.1፣ 7-101፣ እና 7-301፣ COMAR 13A.02.06 እና 13A.05.09

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** በተግባር ላይ የዋለው በውሳኔ ቁጥር 366-87 ነው፣ ጁላይ 14/1987 በውሳኔ ቁጥር 65-92 ተሻሽሏል፣ ጃኑወሪ 27/1992 በውሳኔ ቁጥር 328-04 ተሻሽሏል፣ ጁን 8/2004 በውሳኔ ቁጥር 239-11 ተሻሽሏል፣ ሜይ 10/2011 እንደገናም በውሳኔ ቁጥር 414-18፣ ሴፕቴምበር 11/2018 እንደገና ተሻሽሏል።